# በትጋት ስሩ

*ፕሬዘደንት ሔንሪ ቢ. አይሪንግ*
*የቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ*

*ወንድሞች ሆይ ዛሬ ምሽት ከናንተ ጋር በመሆነ ምስጋና ይሰማኛል። በማውቀው የክህነት አገልግሎታችሁ ርህራሄ ይሰማኛል። ዛሬ ምሽት ስለ ጌታ አገልግሎት ትጋት እናገራለሁ። የቅርብ ልምድ ይህን እንድመርጥ አድርጎኛል።*

*አንዱ አስደናቅ ስለሆነው አሮናዊ ክህነት መፅሄት ትናት ነው። አርዕስቱ የእግዚአብሄር ግዴታ ሥራ ይላል። በማንበብ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ሳሰላስል ፕሬዝዳንት ብርገም ያንግ ለክህነት ሥልታን ያዥዎች ቃል የገባውን የሚያስረዳ መሆኑን ተገነዘብኩኝ።*

*"የክህነት ሥልታን በመያዝ የሚካፈሉ ግለሰቦች እና በታማኝነት አገልግሎትን የሚቀጥሉ እና በህይወታቸው ሁሉ ማንኛውንም ግዴታ የሚፈፅሙ የመቀበል ዕድል ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ነገር እንዴት ለመቀበል እንዳላቸው እውቀት በማግኘት የእግዚአብሄርን ሀሳብ ያለማቋረጥ ልያውቁ ይችላሉ።*

*በጥቂት ስምንታት በፍት አድስ ድያቆን ይህን የትጋት መንገድ መጀመሩን አየሁ። አባቱ ልጁ የሳለውን የቻፕል መስመርን አስየኝ፤ ይህም ቁርባን የሚያሳልፉትን ድያቆኖች ቁጥር እና ድርሻ የሚያሳይ ነበር። አባቱና እኔ ልጁ ሳይጠየቅ የክህነት ስልጣኑን ለማሳካት ይህን በማድረጉ ሳቅን።*

*ከእግዚአብሄር ግዴታ ሥራ መፅሄት ምሳሌ ትጋቱን ተገነዘብኩኝ። እግዚአብሄር የሚፈልግብህን በመማር ባወትችሁት ዕቅድ በትጋት ከሰራችሁ እና ልምዳችሁ እንዴት እንደለወጣችሁ ሌለሎች በማካፈል ልትባርኳቸው ትችላላችሁ።*

*ድያቆኑ ይህን ሥዕል ያነሳው የጌታን ጥሪ ለመሥራት እርግጠኛነቱን ለማረጋገጥ ነው። በክህነት አገልግሎቱ መጀመሪያ እግዚአብሄር ያስፈለገውን እንድሰራ ጌታ በታጋት እንድቀጥል አስተማረው*

*ዛሬ ምሽት ስለ ትጋት እንድናገር ያደረገኝ ሌላኛው ልምድ አንድ ሰውን በህይወቱ መጨረሻ የክህነት ሥልጣን አገልግሎቱን ማየት ነበር። ሁለ ጊዜ ቆጳስም ሆኖ ነበር። የመጀመሪያ የቆጳስነት ሹመቱ ወጣት በነበረ ጊዜ ነበር። አርጅቶ ከሁለተኛው ቆጳስነት ወርዶ ነበር። አካላዊ አቅሙ ስላልቻለ ለአገልግሎቱ በጣም አስቸጋሪ ነበር።*

*ብሆንም በትጋት ለመፈፀም ዕቅድ አለው። በየሳምንቱ ብዙ ሰዎች በሚመቱበት መግቢያ በር አከባቢ ይቀመጣል። መቀመጫውም እንዳይያዝ በቅድሚያ ይሄዳል። የሚመጡት ሰዎች ሁሉ ልክ ቆጳስ በነበረበት ወቅት ፍቅሩን እና አስተናጋጅነቱን ይመለከታሉ። ለማገልገል የከፈለው ዋጋ እና ተፅዕኖው ምክንያት ሞቅ ባለ እንዳነሳን  እናውቃለን። የቆጳስነት ሥራው ቢያልቅም የክህነት ሥልታን አገልግሎቱ አላለቀም።*

*የዝህ አይነት ምሳሌ አገልጋዮችን አይታችዋል። ዛሬ ምሽት ስለነሱ የተማርኩትን እነግራችዋለሁ። ለማን አገልግሎት እንደሆነ እና ለምን አላማ እንደሆነ ይጀምራላ።ይህ ወደ ልባቸው ከገባ ልዩነትን ያመጣል።*

*መጀመሪያ አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያዥ ለሆኑት ወጣቶች በቀጥታ እናገራለሁ። እግዚአብሄር በናንተ ላይ ያደረገውን እምነት ሠማችሁ የበለጠ ትጋት ይኖራችዋል። በእግዚአብሄር ሥራ ግዴታ መፅሄት ውስጥ ከተቀዳሚ አመራራት ለናንተ መልዕክት አለ።*

*የሰማይ አባት በናንተ ታላቅ እምነትና እርግጠኝነት ስላለው የሚታሟሉ ተልዕኮ አለው። በፀሎት ወደ እሱ ስትዞሩ ይረዳችዋል። ለመንፈስም አዳምጡ።  ትዕዛዛትን በመጠበቅ የገባችሁትን ቃል ኪዳን ጠብቁ።*

*መጥመቁ ዮሀንስ የያዛችሁትን የክህነት ሥልጣን እንደገና ለመመለስ ወደ ምድር ተመልሰው ነበር። እሱም የአሮናዊ ክህነትን የያዘ ነው። እየሱስንም ለመጠመቅ ወደ ዮሀንስ ነው የዞረው።*

*የአሮን ክህነት የመላዕክት አገልጋይን ቁልፍ ፣ የንሰሀ ወንጌል እና ለሀጥያት በመጥለቅ ጥምቀት እና በግንቦት 15 ቀን 1829 ዓ/ም ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦልቨር ካውደርን እንድካናቸው ጌታ እንደላከው  ዮሀንስ ያውቅ ነበር። ምን ጥሪ እንዳደረገለት እና ለምን አላማ እንደተላከ ያውቅ ነበር።*

ዛሬ የክህነት ሥልጣናችሁ የጌታን ቁርባን ለቤተክርስትያን አባሎች እንድታሳልፉ ያደርጋችዋል። ይህ ሀይል ነው አዳኝ በአካላዊ ትምህርቱ ለአስራ ሁለተኛ ሀዋሪያዎች የሰተው። ከትንሳኤውም በኋላ ቤተክርስትያኑን እንድመሩ ለአሥራ ሁለተኛ ሀዋሪያዎች እንደገና ሰጥተዋል።

በመፅሀፈ ሞርሞን እንደተጠቀሰው ጌታ እራሱ ወሰን የሌውን መስዋዕት ምልክት በማዘጋጀት ለሰዎች ሰትተዋል። የክህነት ሥልጣናችሁን ስትፈፅሙ እንዴት ክብር እንደሰጣችሁ አስቡ። ስታስታውሱት በተቻላችሁት መጠን አገልግሎታችሁን እንደ እሱ በታማኝነት ትወጣላችሁ።

ይህም በኑሮያችሁ ምሳሌ በመሆን ጌታ ላዘጋጃችሁ ማንኛውም የክህነት ሥልጣን አገልግሎት ትጋት እንድኖራችሁ ሀይል ይጨምርላችዋል። ይህ ቆራጠኝነት መልካፃድቅ ክህነትን እንድትቀበሉ ያዘጋጃችዋል። ይህም በጥንት ጊዜ ከግዚአብሄር ልጅ በኋላ የተሰጠ ክህነት ነበር።

አሁን የመልከፃድቅ ክህነት ሥልጣን ለተሰጣቸው ለመናገር ምኞቴ ነው። እንደ አሮናዊ ክህነት መልከፃድቅ ክህነት ከእምነት የበለጠ ጌታ የሚያደርገውን ማድረግ ነው። እንደ እሱ ለመሆን ግብዣ ነው። ቅል ኪዳኑም ይህ ነው፡

የተናገርኩትን ሁለቱን የክህነት ስልጣን ለመቀበል ታማኝ የሆነ እና ጥሪውን የተወጣ አካላቸውን ለማደ በመንፈስ ይነፃሉ።

የሙሴ እና የአሮን እና የአብረሀም ዘሮች እና የቤተክርስትያን መንግስት እና የእግዚአብሄር ምርጮች ይሆናሉ።

እናም ይህን የክህነት ሥልጣን የተቀበል ይቀበለኛል አለ ጌታ።

ለዚህም አገልጋዬን የተቀበለ ተቀብሎኛል።

የተቀበለኝ አባቴንም ተቀብለዋል ።

አባቴን የተቀበለው መንግስቴ ሰማያቴን ይቀበላል። ስለዚህ አባቴ ያለው ሁሉ ይሰጣቸዋል።

ይህ ሁሉም የክህነት ሥልታን ያዥዎች ለዕንቁ በረከቶች ከፍ የሚደረጉበት ምሳሌ ነው። በመጽስሀፍ ቅዱስ ጌታ ለኛ ምሳሌ የሰጠን በትምህርትና ቃኪዳን አንቀጽስ አንድ መቶ ሰባት ነበር።

ስለዚህ አሁን እያንዳንዱ ሰው ግዴታውን በመማር የተሾመበትን የሥራ ድርሻ በሁሉም ትጋት ይወጣ።

ሰነፍ የሆነው እና የሥራ ግዴታውን የልተማር ብቁ ሆኖ ልቆም አይችልም።....

ሥራችን ከጌታ በመማር በሁሉም ትጋት መፈፀም እንዳለብን እንጂ በፍፁም ሰንፍ መሆን አያስፈልግም። ምሳሌው ቀላል ብሆንም ለመከተል ቀላል አይደለም። በቀላሉ እንረበሻለን። በየቀኑ ዜናን ማጥናት ከክህነት ሥልጣን ትምህርት የበለጠ ፍላጎት የሚያሳድር ይመስላል። ቁጭ ብለው ማረፍ የክህነት አገልግሎት የሚፈልጉትን ከመንብኘት የበለጠ ልስብ ይችላል።

እራሴን ከክህነት ሥልጣን ሥራ በሌላ ፍላጎት የሚወግደኝ እና ሰውነቴ እርፍት ስፈልግ ይህን የጨሄት ለቅሶን ለራሴ እሰጣለሁ። እሱን አስታውሱ።  ጌታ በክህነት ስለጣን ትጋትፍፁም ምሳሌያችን ነው። እስ ሻምበላችን ነው። በፍታችን ይሄዳል። እንድንከተለው መረጠን እናም ሌሎችን ከኛ ጋር እንድናመጣም አደረገ።

ዛሬ ምሽት አስታውሰዋለሁ እናም ልቤን ያማስላል። ይህ ማስታወስ ያለብን ከትንሳኤው በፍት ቅዳሜ ምሽት ነው። ምሳሌውን ከቀኑ በፍት አስታውሳለሁ።

ለአባቱና ለኛ ፍቅር ብሎ ከሚችነት ሰው በላይ እራሱን ለስቃይ ዳርገዋል። ወሰን የሌለውን መስዋዕትነቱን  ነግሮን ነበር።

እነሆ እኔ እግዛብሄር ለሁሉም ይህን ስለተሰቃየሁ ንሰሀ ከገቡ ልሰቃዩ አይችሉም።

ግን ንሰሀ ካልገቡ እንደ እኔ መሰቃየት አለባቸው።

እኔ እግዚአብሄርን እንኳ ታላቅ የሆነ ስቃይ ደርሶብኛል፤ በህመም ምክንያት ከሰውነቴ እንደ ላብ ደም እየወጣ አካሌን እና መንፈሴን አስቃይተዋል።...እናም ቆምጣጣውን ዕዋ በመጠጣት መኮማተር የለብኝም....

የሆነ ሆኖ ክብር ለእግዚአብሄር ነው፤ እኔ በመቋደስ ለሰው ልጆች ዝግጅቴን ጨረስኩኝ።

በካልቨር መቀል ላይ ሆኖ ጌታ አስታወቀ፤ አለቀ አለ። ከዚያ መንፈስ አካሉን ለቀቀ እና የቀረው አካሉ በፍቅር ተቀበረ። ከትንሳኤው በፍት በወህኒ ነፍሳት ለሶስት ቀን አስተምሮን ነበር። ለአገልግሎቱ ከባድ ሥራ ጨርሻለሁ የሚል ስሜት ሠማኝ ይህን አስታውሳለሁ።

የጌታ ምሳሌ ወደ ፍት እንድጓዝ ብርታት ይሰተኛል። የምድር ሥራው ብያልቅም ግን ነፍስን ለማዳን ወደ ወህኒ ነፍሳት ሄደዋል። የታማኝ መንፈሶች ሥራ በማደራጀት በሀጢአት ክፍያው ምህረት የሚደረግላቸውን ለማዳን አቻለ።

ግን እነሆ ከፃድቃኖች ሀይሉን በማደራጀት መላዕክተኞችን ሀይል አልብሶ ሾማቸው፤ እናም በጨለማ ውስጥ ላሉት የወንጌል ብርሀን እንድወስዱላቸው አዘዛቸው፤ ለሁሉም የሰው ልጆች መንፈስ እና ለሙታንም ወንጌል ተሰብከዋል።

የተመረጠው መላዕክት የጌታን ቀን በይፋ ለማወጅ ወደ ፍት በመሄድ ለምርከኞች እና ለሀጢአታቸው ንሰሀ በመግባት ወንጌልን ለተቀበሉ ሁሉ እንኳ ነፃነትን አወጀ።

እሱን በሚናስታውስ ጊዜ ፈተናን ለመቋቋም ቀላል ይሆናል። ዛሬ እሱን ስላስታወስን ሀላፍነታችን ለመማር እና ቃል የገባነውን ቃል ኪዳን በሁሉም ትጋት ለመስራት ቆርጠናል። በምሳሌው ምክንያት በዚህ ህይወት የስጠንን ፍተናዎች እስከ መጨረሻ በመወጣት የአባቱን ፍቃድ እሱ እንዳደረገ ለዘላለም እናደርጋለን።

ይህ የጌታ ቤተክርስትያን ነው። ድክመት እንዳለብን ብያውቅም በእምነት ሾመን። በታማኝነት አገልግሎት እና በሀጢአት ክፍያው እሱ የሚፈልገውን በማድረግ የሚናገለግላቸውን መባረክ እንችላለን። በትጋት ለረጅም ካገለገልን እንለወጣለን። ከመቸውም የበለጠ እንደ እሱ እንሆናለን።

በአገልጋዮቹ ኑሮ የተአምር ማስረጃን አይቻለሁ። ባለፈው ጥቂት ሳምንት ታማኝ የሆነ የክህነት ሥልጣን ያዥ ቤት አይቻለሁ።

እንደ ዲያቆን፣ አባት፤ ቆጳስ እና የስቴክ አመራራት እንደሆነ አውቀው ነበር። በክህነት ስልጣኑ የእግዚአብሄር ልጆችን በትጋት መገልገሉን ለአስር ዓመታት ተመልክቻለሁ።

ቤተሰቦቹ ከቦውት ነበር። ሙሉ ልብስ ከከረባት ጋር በመልበስ ይስቅ ነበር። ህክምና ላይ እንዳለ ስለተነገረኝ ተገረኩኝ።

በክህነት ሥልጣን አገልግሎቱ በመቶ የሚቆጠሩ እንግዳዎች ሰላም እንዳለ እኔንም አስተናገደኝ። እሱ ያለበትን መከራ ልረዳው ሄድኩኝ፤ ግን አንዳንዴ በክህነት አገልግሎት እንደምሆን እኔ እርዳታ ተደረገልኝ እናም ተማርኩኝ።

ቅጭ ብለን አወራን። አባቱ እናቴ ሞት ስቀርባት እንዳስተናገዳት ነገረኝ። ይህን አላወኩም ነበር። በልጅነት ከአባቱ እንደተማረ ተገነዘብኩኝ። ይህ ሀሳብ ልጄን ከኔጋር ወስጄ ሌሎች በማፅናናት ለባረኩት ምስጋና እንዳስገባ አደረገኝ።

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ጥየቀ፡ በረከት እንድትሰጠኝ ብጠይቅ ተገቢ ነው? የቅድሞ ስቴክ ፐሬዝዳንቱ እራሱን በመልከፃድቅ የክህነት ሥልጣን ሀይል በዘይት ቀባው።

በርከቱን በቃል ኪዳን ሳሽግ ጌታ ለዚህ ታማኝ የክህነት ሥልጣን ያዥ የደረገውን በመንፈስ ቅዱስ ተማርኩኝ። ንፁህ ስለነበር ሀጢአቱ ታጥበዋል። ተፍጥሮአዊነቱ ጌታ ወደሚፍልገው ተለወጠ። የሞት ፍርቻ የለውም። የልቡ ፍላጎት ቤተሰቡን እና የሰማይ አባት ልጆችን ማገልገል ነበር።

የጌታ ርህራሄ ትጋት ላለው የክህነት አገልጋዩ ላይ በማየቴ በምስጋና ምሽት ወጣሁኝ። ልባቸውን ወደምፈልገው በመለወጥ እሱ እንደሚያደርግ ያደርጋቸዋል።

ለጌታ የክህነት ስልጣን አገልጋዮች በዚህ ምክር እዘጋለሁ። በትልቀትና በትጋት መፅሀፍ ቅዱን እና የኗሪ ነቢይ ቃልን አስላስሉ። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሄርን አባትን እና የተወደደ ልጁን ተፍጥሮአዊነት እንድድገልፅላችሁ በፀሎት ቋም ሁኑ። መንፈስ ጌታ የሚፈልገውን እንድያሳያችሁ ተማፀኑ። ለመስራት ዕቅድ አድርጉ። ታዛዥ ለመሆን ቃል ግቡ። እሱ የጠየቀውን እስከምትፈፅሙ በቁርጠኝነት አድርጉ። ከዚያ በኋላ ለማገልገል ዕድል ስለሰጣችሁ እና ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለማወቅ በፀሎት አመስግኑ።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ኗሪ መሆናቸውን እመሰክራለሁ። ከትንሳኤ የተነሱ ህያው ፍጡር ኖኖ የሚወዱን ናቸው። የክህነት ሥልጣን ቁልፍ በሰማይ መላዕክት ለነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ተሰትተዋል። ባልተሰበረ መስመር ለፐሬዝዳንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን ተሰጥተዋል። ይህም ቁልፍ በያንዳንዱ ኗሪ ሀዋሪያዎች የተያዘ ነው።

**የመንፈስ ብዛት እምነት እንድሰማችሁ  እና በጌታ እውነተኛ ቤተክርስትያን  የክህነት አገልጋይነት በመካን የተቀበላችሁትን ቃል ኪዳን በረከተን እተውላቸዋለሁ።፡**

**በተቀደሰው ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።**